የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፶፩
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፭ ቀን ፪ሺ፰ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.51
ADDIS ABABA,24th March ,2016

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፹/፪ሺ፰ ዓ.ም

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ (ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ---------------------------------ገጽ፰ሺ፱፻፴፬

## CONTENT

Regulation No. 380/2016

Agricultural Transformation Council and Agency Establishment Council of Ministers Regulation (Amendment) Regulation ----------------------------page 8934

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፹/፪ሺ፰

### የግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና ኤጀንስ ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና ፴፱ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፤

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ (ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፹/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ማሻሻያ**

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፰/፪ሺ፪ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

፩/ የደንቡ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) ተሰርዞ ነባሮቹ ፊደል ተራ (ሐ) እና (መ) ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) ሆነው ተሸጋሽገዋል።

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 380/2016

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE AGRICULTURAL TRANSFORMATION COUNCIL AND AGENCY ESTABLISHMENT REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and 39 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916 /2015;

1. **Short title**

   This Regulation may be cited as the "Agricultural Transformation Council and Agency Establishment Council of Ministers (Amendment) Regulation No. 380/2016".

2. **Amendment**

   The Agricultural Transformation Council and Agency Establishment Council of Ministers Regulation No. 198/2010 is hereby amended as follows:

   1/ Paragraph (b) of sub-article (1) of Article 4 of the Regulation is deleted and the existing paragraph (c) and (d) are reorganized as paragraph (b) and (c).

   2/ sub-article (1) Article 6 of the Regulation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

፪/ የደንቡ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ(፩) ተሠርዞ ፰ሺ፱፻፴፮ ...ው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፦

"፩/ ምክር ቤቱ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፤ አስፈላጊ ሲሆን በሰብሳቢው ሲጠራ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡"

፫/ የደንቡ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፦

"፪ ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡"

፬/ የደንቡ አንቀጽ ፲ ከንዑስ አንቀጽ (፪) እስከ ንዑስ አንቀጽ (፱) ያሉት ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ ንኡስ አንቀጾች (፪)፣ (፫)፣ (፬)፣ (፭)፣ (፮)፣ (፯) እና (፰) ተተክተው ነባሮቹ ንዑስ አንቀጾች (፲ እና (፲፩) ንዑስ አንቀጾች (፱) እና (፲) ሆነው ተሸጋሽገዋል፦

"፪/ የሰብልና እንስሳት ሀብት ግብርና ምርትና ምርታማነት መሠረታዊ የአሠራር ሥርዓት ማነቆዎችን በጥናት እንዲለዩና የሚፈቱበት ስልት እንዲነደፍ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፫/ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን ግብይት ለማሳደግና እሴት ለመጨመር የግብርና ንግድና ግብይትን መሠረታዊ የአሠራር ሥርዓት ማነቆዎችን በጥናት እንዲለዩ ያደረጋል፤ የመፍትሄ ሀሣብ ያቀርባል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፬/ ዘላቂና አሳታፊ የሆነ የአካባቢ ጥበቃና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ መሠረታዊ የአሠራር ሥርዓት ማነቆዎችን በጥናት በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ያቀርባል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፭/ ግብርናን አስመልክቶ የሚከናወኑ ሥራዎችን በአግባቡ ለመፈጸምና ለመቆጣጠር የሚያስችል ተቋማዊ አቅምን ለማሳደግ መሠረታዊ የአሠራር

"1/ The Council shall hold regular meetings twice in a year; and extraordinary meetings at any time when called by the Chairperson."

3/ Sub-article of (2) Article 7 of the Regulation is deleted and replaced by the following new sub-article (2):

"2/ The Agency shall be accountable to the Ministry of Agriculture and Natural Resource."

4/ Sub article (2) to sub-article (9) Article 10 of the Regulation is deleted and replaced by the following new sub-articles (2), (3), (4), (5), (6), (7) and (8) and, the existing sub-articles (10) and (11) are renumbered as sub-articles (9) and (10):

"2/ Identify, through study, the basic systemic bottlenecks of agricultural production and productivity of crop and livestock; recommend and follow up implementation of same;

3/ Identify, through study, the basic systemic bottlenecks of agri-business and agricultural marketing to increase marking and value addition of agricultural products for domestic and export markets; recommend and follow up implementation of same;

4/ Identify, through study, the basic systemic bottlenecks to ensure environmental sustainability, inclusiveness and food security of agricultural production; recommend and follow up implementation of same;

5/ Identify, through study, the basic systemic bottlenecks of developing enhanced institutional capacity for implementation and monitoring of agricultural interventions; recommend and follow up implementation of same; 8936

6/ Develop a prioritized list of deliverables that can catalyze agricultural transformation for focused implementation;

ሥርዓት ማነቆዎችን በጥናት እንዲለዩ ያደርጋል፤ የመፍትሄ ሀሳብ ያቀርባል፤ አፈጻጸሙንም
፰ሺ፱፻፴፯
[illegible]ል፤

፮/ የግብርና ትራንስፎርሜሽንን ለማቀላጠፍ በትኩረት የሚፈፀሙና ቅድሚያ የተሰጣቸው ተግባራትን ዝርዝር ያዘጋጃል፤

፯/ በግብርና ትራንስፎርሜሽን አጀንዳ መሠረት ከምክር ቤቱ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ፕሮጀክቶችን ያስተዳድራል፤ ይመራል፤

፰/ የግብርና ልማት አፈጻጸምን ውጤታማነት ለማረጋገጥ በግብርና ተዛማጅ ተቋማት እንዲሁም የግብርና ልማቱን ለመደገፍ በሚቀረፁ ፕሮጀክቶች መካከል መልክዓ ምድር መሠረት ያደረገ ጠንካራ ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፤"

፭/ የደንቡ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ለ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ለ) ተተክቷል፦

"(ለ) የኤጀንሲውን ሠራተኞች የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረታዊ መርሆዎችን ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤"

## ፫ ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት ፲፭ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

**ኃይለማርያም ደሣለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

7/ Manage and lead projects of specific deliverables within the agricultural transformation agenda as requested by the Council;

8/ Create strong linkages among agricultural and related institutions and projects in specific geographies in order to ensure the effectiveness of agricultural development activities;"

5/ Paragraph (b) of sub-article (2) of Article 12 is deleted and replaced by the following new paragraph (b):

"b) employ and administer the employees of the Agency in accordance with directives approved by the Government following the basic principles of the federal civil service laws;"

## 3. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 24th day of March , 2016.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**